# ኢትዮጵያና  የዘረኝነት ልክፍት

ሓጎስ ኣረጋይ (PhD)                    ቀን ሰኔ 2/2009ዓ/ም

መወለድ    የምርጫ ጉዳይ ኣይደለም ። የሰው ልጅ መወለድን  እንጂ የመጣበትን ሃረግ የመወሰን ስልጣን የለውም። ስለዚህ ለመግባባት፣ ኣብሮ ለመኖር  ፣ወዘተ፣  ሰው መሆን ብቻው  በቂ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱ  ሰው፣ ሰው ሁኖ ወደዚች ኣለም ብቅ ይላል እንጂ  ትምክህተኝነት፣  ዘረኝነት፣  ብሄርተኝነት፣  ደግ፣  ክፉ    ወዘተ  የሚሉት  ሃሳቦች ኣያውቃቸውም።  ከላይ  የተገለፁት  ተቀፅላዎች   ከማህበረ  ሰብ  በሚያደረገው  ግንኙነት የሚያድጉና የሚያቈጠቁጡ ናቸው።   ነገር  ግን  ጥቅም   የሚባለው  ነገር  በግለ  ሰቦች ደረጃም  ቢሆን ልዩነት እንዲፈጠር ያደርጋል። ልዩነት መኖር ባህርያዊ ነው፣ ነገር ግን ልዩነቱን የምንፈታበት ወይም የምናጠብበት ዘዴ ፍትሃዊ ካልሆነ  ወደ ቅራኔ ያመራል። ከዚያም ኣልፎ ሁኔታው ወደ ማህበረሰብ ፣ መንግስታት ወዘተ ሊያድግ ይችላል።

የጥቅም  ጉዳይ  ሆኖ  ኢትዮጵያን  ማእከል  ኣድርገው   የተለያዩ  ሰዎች  የተለያዩ ኣስተያዬቶች ሲሰጡ ይስተወላል። የሚነሱ ሃስቦች መሰረት የሚያደርጉ ፣ ኣገር ልትፈራርስ ናት፣ ዘረኝነት ነግሰዋል፣ የኣንድነት ስሜት ጠፍተዋል፣ ወዘተ ። ስለዚህ በዚች ኣጭር ፅሁፍ  የማተኩረው በዘረኝነት ላይ ኣንዳች ነገር ለማልት ፈልጌ ነው ። እንደ መነሻ ይሆነን ዘንድ ጥያቄዎች ላንሳ፣

1. ዘረኝነት (racism) ምን ማለት ነው?
2. ኣንድን ሰው ማህበራዊ ተግባቦቱ ከብሄሩ  ማህበረሰብ የተወሰነ እንደሆነ  ዘረኛ ልንለው እንችላለን?
3. ማነው በኢትዮጵያ የዘረኝነት ልክፍት የሚያንፀባርቀው ?

## 1. ኢትዮጵያና ህዝቦቿ

ኢትዮጵያውያን  እንደ ጀርመን ፣ እንግሊዝ  የመሳሰሉት  ኣገራት የኣንድ ብሄር ወይም የኣንድ  ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ኣይደለንም። ወደ ሰማንያ የሚያህሉ ብሄር/ ብሄረ ሰቦች እና ህዝቦች  ሰብስብ ነን።  ስለዚህ  ኣንድ ሰው ከኣንድ በሄር/ብሄረ ሰብ  መወለዱ ኣይቀሬ ነው። በመሆኑም

- በአግባቡ ከተጠቀምንበት፣ ህብረብሄራችን ድምቀታችን ፣ ውበታችን የእድገት መሳልላችን ይሆናል። ምክንያቱ የተለያዩ አመለካከቶች ፣ የባህል እሴቶች ወዘተ ለእድገታችን መሳልል ሁነው ስለሚያገለግሉን፣
- በአግባቡ ካልተጠቀምንብት ደግሞ ለውድቀታችን መሰረት ሊሆኑ ይችላሉ

ብዙህነት ባለብት አገር የተለያዩ አመለካከቶች ሊኖሩ ግድ ይላል። ከዚህም የሚመነጭ ይመስለኛል የተለያዩ ሰዎች ዘረኝነትን በተለያዬ መልኩ ሲገነዘቡት/ሲያስተጋቡ ይደመጣሉ። እያንዳዳችን ከአንድ ብሄር/ብሄረስብ ወይም ጥምር ግንድ ያለው ሃረግ ነው የመጣነው። የዘረኝነት ትርጉም እንደፈለግን የምንገነዘበውና የምንጠቀምበት ከሆነ፣ እንዲሁም በሰበብ አስባብ አንዱ ተንስቶ ለሌላኛው ዘረኛ የሚለው ከሆነ፣ ዘረኛ ያልሆነ ሰው በአገራችን የለም ማለት ነው። ስለዚህ በፍረጃ ብቻ እርስ በእርስ ከተወነጃጀልን ወደ መልካም ነገር አይወስደንም ፣ ማህበራዊ ተግባቦትን ያዳክማል ወዘተ ብዬ አምናለሁ። በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ፣ በአሁኑ ሰአት አንዱን ሌላውን መጨፍለቅ የማንችልበት ግዜ ደርሰናል። ስለዚህ ከእንደዚህ አደጋ ለመላቀቅ የዘረኝነት ገፅታና ባህርይ ማወቁ ለመፍትሄው ግማሽ ያህል መንገድ መጓዝ ነው ብዬ አምናለሁ። መታወቅ አለበት ብዬ እማስበው ግን ፣ በየተኛው መለኪያም ቢሆን፣ አንድን ህዝብ እንደ ህዝብ ዘረኛ ብሎ መፈረጅ የውድቀት መጀመርያ ነው ብዬ አምናለሁ ።

ይህን ሃሳብ ለማንሳት የፈለግኩበት ምክንያት በአለማችን ዘረኝንት ታይተዋል ይታያልም። መዘዙም እጅግ የከፋ ሁኖ አልፈዋል። ለወደፊትም በትክክል አውቀን ማስተካከል መቻል ያለብን ይመስለኛል። ስለዚህ በቅድሚያ የዘረኝነት ባህርይ እና ገፅታ ምን እንደሚመስል ማየቱ መልካም የመስለኛል።

## 2. የዘረኝነት ገፅታና ባህርይ

የዘረኝነት ባህርይ፣ ገፅታ ና ምንነት ለማየት ይቻል ዘንድ ታሪካዊ መሰረት ያላቸው ጥያቄዎች ባስቀድም ጥሩ ይመስለኛል ። ስለዚህ

- የጀርመን ናዚ ወይም ‘ሂትለር’ ምን ልንለው እንችላለን ?
- የሂትለር ገፅታዎችስ ምን ነበሩ ?
- ሂትለር በተከተለው ርዕዮት በአለማችን ምን አስከተለ? ውጤቱስ ምን ሆነ?

ሂትለር በነበረው ርዕዮት በጀርመን ኣገር ይኖሩ ከነበሩ 6000000 የሚያህሉ ኣይሁዳውያን መካከል ብዙ ሰው በግፍ መጨጨፉን ታሪክ ያስረዳል። በስተመጨርሻ ድል ባያደርግም በወቅቱ ኣለምን ለማመሰቃቀል ችለዋል ። ስለዚህ ሂትለር በኣለማችን ኣስከፊው የዘረኝነት ኣባዜ የተጠናወተው ሰው እንደነበር ብዙዎቹ ይስማማሉ። በመሆኑም በኣለም ደረጃ ከሂትለር ጎን ተሰልፈው የነበሩ ወደ ፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ ስምምነት ተደርሰዋል ።ሆንም ግን ዘረኞች የምንላቸው ሂትለርና ተከታዮቹ ናቸው እንጂ መላ ጀርመናውያን ኣይወክሉም የሚል እምነት ኣለኝ። በመሆኑም ፣ በኣሁኑ ሰኣት ጀርመናውያን ከኣውሮፓ ሃገራት መካከል ብዙ የተቸገሩ ስደተኞቹን በመቀብል ታሪክ እየሰሩ ይገኛሉ። እንዲሁም ኣብሮ ለመስራትና ለማደግ ከኣውሮፓ ሀብረት በጋራ እየሰሩ የሚገኙ ህዝቦች ሁነዋል ።

ዘረኝነት በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በሌላ መልክም ሊገለፅ ይችላል። ለምሳሌ በኣውሮፓ የእግር ኳስ ጨዋታ ኣውሮፓውያን ለኣፍሪካውያን ማንነታቸውን መሰረት ኣርጎ በመሳደባቸው የዘረኝነት ክስ ተመስርቶ የሚተላለፍው የቅጣት ውሳኔ የዘወትር መዝሙር ነው ብል ማጋነን ኣይሆንም ። ስለዚህ

- የዘረኝነት (racism) መገለጫውና ባህርዩ ራስን ኣግዝፎ የማየት ኣባዜና ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ኣንኳስሶ መመልከት፣ ጉዳት ማድረስ ፣ በዘር ነክና ከዘር ተያያዥነት ያላቸው ስድቦች፣ ዛቻዎችን ማድረስን ብለን ማጠቃልል ይቻላል።
- Racism is a prejudice, discrimination, or antagonism directed against someone of a different race based on the belief that one's own race is superior (https://www.google.com/#q=definition+of+racism)

ከላይ በተገለፀ መሰረት፣ ዘረኝነት በኢትዮጵያ ታይተዋልን? እየተሰራበት ነውን ? የሚለው ጥያቄ ለመመልስ እሞክራሎህ።

### 3. ኢትዮጵያና ዘረኝነት

የዘረኝነት ገፅታዎች ከላይ በገለፅኩት መሰረት ከሆነ፣ በኢትዮጵያ ዘረኝነትን እንዴት ልንገልፀው እንችላለልን ? የዘረኝነትና ዘረኝነት ትርጉም ያላቸው ኣስተሳሰቦችና ድርጊቶች በኣገራችን በተለያዬ ወቅት የተለያዩ ቅርፅና ይዘት ይዘው ሲንፀባረቁ ይስተዋላሉ። ኣንዳንዴ ብሄርተኛ የሆነውን ሰው ዘረኛ ሲባል ይሰማል። ኣንዳዶቹ ደግሞ የዘረኝነት ኣባዜ ኑሯቸውም በቁመናቸው ልክ ሳይመዘኑ ይቀራሉ።

ስለዚህ እነዚህን መልክ ለማስያዝ በመፅሃፍ ደረጃ የተፃፉ ፣ በድራጊት የተገልፁ ፣ በመሪዎችና በፖለቲከኞች ደረጃ የተነገሩትንና አባባሎች ለመገለፅ እወዳሎህ። በእርግጥ የተፃፉትን፣ የተነገሩትንና በድርጊት የተፈፅሙ ሁሉ እዚህ እዘረዝራሎህ ማለት ግን አይደለም። ለማሳያነት ያህል ግን አንዳንዶቹን ለመጥቀስ እሞክራሎህ። ከዚያ በኋላ አንባብያን የተዘረዘሩትን በመነሻነት ወስደው የራሳቸው አክለው ማን ነው የዘረኝነት አባዜ የሚንፀባረቅበት በሚለው የራሳቸው ፍርድ መስጠት ይችላሉ። እንደ ግለ ሰብ ደግሞ የራሴን አስተያዬት በስተመጨረሻ አክላሎህ።

### 3.1በደርግ ዘመንና ከዚያ በፊት ይንፀባረቁ የነበሩ የዘረኝነት አስተሳሰቦች

በአፄዎችና ደርጋውያን ይደርስ የነበረው ግፍና ጭካኔ ለማሳያነት ያህል የጭፍጨፋ ድርጊትና የስነ ልቦና ጫና በሚል ተከፍሎ ከዚህ በታች ቀርበዋል።

#### 3.1.1 የጭፍጨፋ ድርጊት

በአፄ ሚኒሊክ ግዜ በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦች ይደርስ የነበረው ጭፍጨፋ ጭካኔ የተሞላበት እንደነበር ብዙዎቹ ይስማማሉ። በወቅቱ ከተፈፀሙት ዘግናኝ ጭፍጨፋዎች መካከል ፣

- ❖ አፄ ምንሊክ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መሆናቸው እንዳሳወጁ ወዲያውኑ ሰራዊታቸው ወደ ትግራይ እንዲዘምት አደረጉ። በዚህ ዘመቻ፣
  - ➢ ልጅ ሽማግሌ ሳይሉ ወንድ የትግራይ ተውላጅ የሆኑትን እዲገደሉ ፣ እንዲሰለቡ ካልሆነም እንዲታረዱ
  - ➢ የትግራይ ህዝብ ንብረት እንዲዘርፉ ካልቻሉ ደግሞ እንዲያቃጥሉ

  ትእዛዝ ማስተላለፋቸው የሚጠቁም የተለያዩ ማስረጃዎች በመጥቀስ በመምህር ገ/ኪዳን ደስታ "እምቢታ አንፃር ወረርቲ " በሚል መፅሃፋቸው ከገፅ 295-311 በዝርዝር አስቀምጠዋል። ይህንን ዘር ለይቶ የጭካኔ ተግባር የፈፀሙት በትግራይ የተለያዩ አካባቢዎች በነበራቸው ረዘም ያለ ቆይታ እንደሆነ መፅሃፉ ያስረዳል። በቆታቸው ግዜም የትግራይ ህዝብ ፍዳውን ያየብት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል።
- ❖ ዶ/ር ሃብተማርያም (1986) የአቶ አፈወርቅ ገብረእየሱስ ዳግማዊ ሚኒሊክ የሚል መፅሃፋቸው በዋቢነት ጠቅሰው እንዳስቀመጡት ፣ ምንሊክ በአጠቃላይ

በትግርኛ ተናጋሪዎች የነበራቸው ጥላቻና ህዝብ እንደህዝብ ለማሰቃየት የነበራቸው አባዜ እንደሚከተለው ተገልፅዋል

- ✓ በአድዋ ጦርነት ላይ ከጣልያን ጎን ተሰልፈው የነበሩ፣ ነገር ግን በኢትዮጵያ ወታደሮች የተማረኩ ቁጥራቸው ከ 400 መቶ በላይ የሚሆኑ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑትን ሰዎች ቀኝ እጃቸውና ግራ እግራቸው ቆረጧቸው . . . .ይላል (ከገፅ 700-715 ይመልከቱ) ። ሚንሊክ ኤርትራን ለጣልያኖች መርቀው በፊርማቸው ያስረከብዋት አገር የነበረች ናት ። ይህን ሲያደርጉ አንደኛ የትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ ለሁለት ለመክፈል ነው ሌላው ደግሞ ከጣልያን መሳርያ ለማግኘት እንደ ነበር ብዙዎቹ ይስማማሉ።
- ✓ በግቤ፣ አዋሽ፣ ከፋ ፣ ሃረርጌ ወዘተ ብዙ የኦሮሞ፣ ወላሞ፣ ወዘተ ህዝብ እንዳለቀ ይገልፃሉ ። የድርጊቱ አስከፊነት ለመግለጽ በወቅቱ ውሻና እርግብም እንዳልቀረ በማሳያነት ይገልፃሉ (ገፅ 677)
- ✓ "ምኒሊክ የሰሎሞን አንበሳ . . . . . የጋላ ድልብ. . . . . ሰለቸውና የትግሬን የአንበሳ ለምድ የለበሰ መስበር ወደደ" ገፅ 680 ላይ እንደተቀመጠው

- ❖ በአማራ ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ግን ከላይ የተጠቀሱ ጭካኔ የተሞላበት አስከፊ ድርጊት አፄ ሚኒሊክ መፈፀማቸው በማሳያነት የሚጥቅስ ፅሁፍ አላገኘሁም።

የደርግን ስንመለከት በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች አረሜናዊ ጭፍጨፋ አካሂደውል። ለምን? መልሱ መሰረታዊ ባህርዩ ስለሆነ ነው።

የደርግ መንግስት በትግራይ ህዝብ ላይ ያደረገው ጭፍጨፋ ግን እጅግ የሚዘገንን መሆኑን የተለያዩ ፀሃፊዎች አስተጋብተዋል። ከነዚህም መካከል የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች በሚል ርእስ በዶ/ር ሃብተማርያም አሰፋ በ 1986 የታተመው መፅሃፍ ላይ ገፅ 680 እና 683-ላይ እንደተመለከተው ደርጋውያን

> "አሳ ከባህር ሲወጣ ውሃ ሳይነካ አይወጣም " "ወይም'
> ደግሞ " አሳን ለመያዝ ውሃን ማድረቅ " የሚል
> መርህ እንደ ነበራቸው ይገልፃሉ።

ከሃረጉ የምንረዳው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ህዝብ ትግራይ (ህወሓት)ን ለማጥፋት የትግራይን ህዝብ ማጥፋት ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ በግልፅ ያሳያል ። በዚህ መርህ መሰረት በኢትዮጵያ በተለያዩ ኣካባቢዎች የሚኖሩትን የትግራይ ተወላጆች የጥቃቱ ሰለባ ሁኑዋል። የተፈፀመው ግፍ በከፊልም ቢሆን እንደሚመለከተው ቀርበዋል፣

- ❖ ደርግ ወደ ገጠር ትግራይ በመዝመት ገበሬውን ወያነ ነህ ብሎ ያሸብራል፣ ንብረቱም ሃብቱም ይዘርፋል፣ ቤቱም ያቃጥላል፣ ሰዎችም ይገድላል። እርጉዞች በሳንጃ ወግቶ ይገድላል። በማእከል የሚታዘዝ ደግሞ በቤኤም ፣ በአውሮፕላን ወዘተ ለ 17 ዓመታት ያህል የትግራይ ህዝብ ተሰቃይተዋል። ይህ ድርጊት በዶ/ር ሃብተማርያም ኣሰፋ (1986) የተፃፈው መፅሃፍ ላይ በሰፊው ተገልፀዋል። ድርጊቱ የቅርብ ግዜ ትዝታም በመሆኑ የኣደባብይ ምስጢር ነው ። ባይኔ ካየኋቸው ኣስደንጋጭ የሆኑ ዲርጊቶች መካከል ደግሞ ለጥቀስ፥

  ደርጋውያን ሌሊት ወደ ኣንድ የገጠር መንደር ዘመቱ ። ከዚያች መንደር ወደ ኣቶ ኣብርሃ ደስታ የተባለ ገበሬ ቤት በመግባት ንብረቱና ራሱን ከገጠር መኖርያ ቤቱ ወደ ሰለክለካ ከተማ (ትግራይ የሚገኝ ከተማ) ኣስረው ኣመጡት። እጁን ወደኋላ ጠፍረው በማሰር ያለምንም ጥያቄ ወዲያውኑ እንዳመጡት በህዝብ ፊት ኣናቱ ላይ በጥይት ፈጠፈጡት።

  በውቅቱ ሰልፍ ማድረግ፣ ድንጋይ መውወር ይቅርና፣ ለደገርጋውያን መስሎ የታያቸው ሁሉ ያለምንም ማስረጃ ከየመንግዱ ፣ ከየቤቱ ወዘተ እያፈሱ ያለ ፍርድ ለእስር፣ እንግልት፣ ሞት ይዳርጋሉ ፣ ይጨፈጭፋሉ ወዘተ

### 3.1.2 ስነልቦናዊ ጫና

በኔ የህይወት ታሪክ ውስጥ ከኣማራ ተውላጆች ጋር ውይይት ኣድርጌኣሎህ። ኣንዳዶቹ ምንድ ነው " የትግርኛ ቋንቋ ጉሮሮ ይከረክራል ይሉኛል" ። ለኔ የሚመሰለኝ የነበረው ኣንዳንድ የትግርኛ ቃላት ወይም ሃረጋት ለመናገር ስለ ሚቸግራቸው/ሚከብዳቸው ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን መፃህፍቶችን ሳነብ ኣነጋገራቸው ከወደ ኋላ ጣጣ እንዳለው ለመገንዘብ ቻልኩኝ። ጉዳዩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፣

- ➢ " የትግሬ ወታደር በዚያ ጉሮሮ በሚፍቀው ቋንቋቸው ኩሪ ኩሪ እያሉ እርጉዝ ኣሰወረዳት እመጫት ጡቷ ደረቀባት. . . . . " ዶ/ር

ሃብተማርያም (1986)  የኣቶ ኣፈውርቅ ገብረ ኢየሱስ ዘብሄረ ዘጌ ጠቅሰው እንዳስቀመጡት (ገፅ 661)

ከዚህ የምንረዳው በፅሁፍ ደረጃ የትግራይን ህዝብ ቋንቋና ባህል የማንኳሰስ ዘመቻ መካሄዱን እንገነዘባለን። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ንግግሮችን /በፅሁፍ ያስቀመጡት ስንመለከት፣

- “ኣፄ ምንሊክ ያደሩበት ኣገር ለምልሞ ሲያድር ትግሬ ያደረበት እንደ ኣንበሳ ልሶት ያድራል “
- “. . . . . ይህ ኣንበጣ ትግሪ በጠፋልን የማይል ኣልነበረም ” . . . .ዶ/ር ሃብተማርያም (1986) የኣቶ ኣፈውርቅ ገብረ ኢየሱስ ዘብሄረ ዘጌ ጠቅሰው እንዳስቀመጡት (ገፅ 661 ይመልከቱ)
- ኣፄ ምንሊክ የትግራይን ህዝብ እንደ ህዝብ የማያዩ እንደ ነብሩ የገብረ ህይወት ባይከዳኝ ጠቅሰው መምህር ገብረ ኪዳን በ ” እምቢታ ኣንፃር ወረርቲ “ መፅሃፋቸው ኣስፍረዋል (ገፅ 512)

ከዚህ የምንረዳው የትግራይን ህዝብ የማንኳሰስ ተግባር በሰፌው ተያይዘውት እንደነበር ለመገንዝብ ኣያስቸግርም። የትግራይን ህዝብ የማንኳሰስ ኣባዜ ሁኖ፣ ነገር ግን በማህበራዊ ግንኙነቱ በትክክል ሳልረዳው ኣንዳንዴም ቀልድ እየመሰለኝ ሳልፈው የነበረ ጉዳይ ነው። ነገር ግን በፅሁፍ የተቀመጠ ከትውልድ ትውልድ ይንፅባረቅ እንደ ነበር በኣሁኑ ሰኣት መረዳት ችያሎህ ።ይህንን ፅሁፍ የምታነቡ ሰዎች ደግሞ የራሳችሁ ምስክርነት መስጠት ትችላላችሁ።

ችጋራም ብሎ እንደ ህዝብ የመፈረጁ ዘይቤ በምንሊክ ግዜ ብቻ ኣላበቃም። በደርግ ጌዜም ከተነገሩት መካከል፣

- ኢትዮጵያችን ችጋራም ተብላ የምትታወቀው ክትግራይ ኣካባቢ በሚመነጭ ችግር ነው። ሰራዊታችን ለኣካባቢው ህዝብ በሶ ፣ ምግብ ባቀረበ ፣ እነሱ ግን ባክሱም ፣ በሽሬ ወዘተ ህዝቡ ራሱ በሰራዊታችን ዘመተ ።

- ከትግራይ የምናገኘው ገቢ ለትግራይ የሚሆን ጠመኔ እንኳን አይሆንም. . . . (መንግስቱ ሃይለማርያም)

እነዚህ አባባሎች  የትግራይ ህዝብ በድጎማ የሚኖርና፣ ራሱ የማይችል፣ ጥገኛ ህዝብ መሆኑን በሃገሪቱ በየተኛውም  አካባቢ የሚኖር የህብረተ/ማህበረ ሰብ ክፍል ላይ አሉታዊ ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ ነው ወይም  ግንዛቤ ለመፍጠር የታለመ ነው። **ነገሩ እውነት ነውን ?**

በኔ እምነት የሰው ሃይል (እውቀት) እንጂ  በከርሰ ምድር ያለው ሃብት  እንደሃብት የምንቆጥር ከሆነ  ከእንስሳዎች  በምን ተሻልን? ፍላጎቴ ባይሆንም  ሳልወድ በግድ ስንዝር የማይራመደውን  የአስተሳሰብ ማእቀፍ ውስጥ ልግባና አንድ ሃሳብ ላስቀምጥ።

> **ትግራይ ደርጋውያንና አፄዎች እንደሚሉት አይደለችም፣ አልነበረችምም። ለምሳሌ ያህል በ 2009 ዓ/ም ከአገሪቱ የወርቅ ልማት 24% ያህል የተያዘው ከትግራይ እንዲሰበሰብ ነው፣ ለዚያውም በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ የሚሰብሰብ ነው።**

*ታድያ ለምንድ ነው ደርጋውያን የትግራይን ህዝብ  ማንኳሰስን የፈለጉት? ነገሩ ግልፅ ነው። ደርጋውያን ከአፄዎቹ በወረሱት አግባብ መሰረት  በትግራይ ህዝብ  የስነ ልቦና ጫና ፈጥረህ ድሃ ነኝ ብሎ እንዲቀበልና  የነሱን ዳርጎት ተመፅዋች ሁኖ  እንደፈለጉት ለማሽከርከር እንዲችሉ ያሴሩት ሴራ መሆኑን እንረዳለን።*

### 3.2 የህወሓት ክስተት ና ጉዞ

የኢትዮጵያ ህዝቦች ከአፄዎችና ከደርጋውያን ጭቆና ግፍ ለመላቀቅ  የተለያዩ የትግል ስልቶች ይጠቀሙ ነበር።  ሁሉንም የትግል ስልቶች በዚች አጭር መጣጥፍ ማስቀመጥ አልችልም። ስለዚህ ወደ ሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በማተኮር የነበረው ሁኔታ ባጭሩ ለማስቀኘት እሞክራለሁ።

**ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ፥**

- **ከሰማይ ዱብ ብሎ በአንድ ጀንበር ወይም በጭሆት/ድንጋይ በመወርወር አይደለም የትግራይን ህዝብ ወኪል ለመሆን የበቃው።**

ቀዳማይ ወያነ የተጀመረው በገበሬ ኣመፅ በሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ነው። ካልኣይ ወያኔ ደግሞ በይፋ የተጀመረበት የካቲት 11/1967ዓ/ም ነው። ለትጥቅ ትግሉ መቀስቀስ ምክንያት የነበረው፣ ደርግና ኣጼዎች በትግራይ ህዝብ ያደርሱት የነበረውን ጭካኔ የተሞላበት ግድያ፣ መስለብ፣ ከኣቅም በላይ የሆነ ግብር፣ የፍትህ መጓደል፣ ራስን የማስተዳደር መብት ማጣት ወዘተ ስለ ኣንገሽግሿቸውና ችግሩን ለመፍታት ደግሞ ትንሽ ቀዳዳም ብትሆን ሌላ ኣመራጭ በመታጣቱ ነው። በወቅቱ የነበረው የችግሩ ደረጃ ለመገንዘብ `

- በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መቐለ ከተማ የሚገኘው የሰማእታት ሃወልትና ሙዝዬም በመጎብኘት ፣
- የመምህር ገ/ኪዳን መፅሃፍ ማንበብ፣
- የዶ/ር ሃበተማርያም (1986) ማንበብ፣
-

እንዲሁም ወደ እልህ ኣስጨራሽ የትግል ስልት ለመግባት ያስገደዳቸው የነበረው ብሄራዊ ጭቆና እና ኣፈና እንደሆነ በተለያዬ መድረክ ተገልፀዋል። ስለዚህ የትግል ስርዓታቸው በደመ ነፍስ ሳይሆን ታስቦበትና ተመክሮበት እንደነበር መገንዝብ ይቻላል። እልህ ኣስጨራሽ የሆነው የሽምቅ ትግል ውስጥ ኣልፈውና ከትግል ኣጋሮቻቸው ጋር በመሆን የደርግን ሰራዊት ለማንበርከክ ቻሉ ። የተነሱበት ዓላማ መሰረታዊ ይዘት በሁሉም የኢትዮጵያ በሄር ብሄረ ስቦች ተቀባይነት በማግኘቱ ነው ።

### 3.2.1 ኣንኳር የህወሓት እይታዎች

ህወሓት በትጥቅ ትግል ግዜም ቢሆን የፕሮግራማቸው ማጠንጠኛ የነበረው፣

- የኢትዮጵያ ብሄርና ብሄረ ሰቦች እኩል ተጠቃሚና ባለመብቶች የሚሆኑበት ስርዓት በኢትዮጵያ መገንባት ነው።
- የኣማራ ገዢ መደብ ከስልጣን መወገድ እንዳለበት የሚል ሰፊ ቅስቀሳና ዘመቻ እንዲሁም የሽምቅ ውግያ ኣካሂደዋል። የኣማራ ገዢ መደብ የገለፁበት ሃረጎች ስንመለከት፣ ነፍጠኛ የኣማራ ገዢ መደብ ፣ ትምክህተኛ የኣማራ ገዢ መደብ የሚሉ ነበሩ።

የእይታው  ዋና ቁም ነገር፣ ብሄራዊ ጭቆና ተገርስሶ በምትኩ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች መብት ከተከበረ ፣ ስርዓቱ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ  መድረሱን  ማረጋገጫ ነው ብለው ያምኑ  ነበር። እውንም አደረጉት

### 3.2.2 የህወሓት ተግባራዊ  ክንውኖች  በትጥቅ ትግል

ህወሓት በትጥቅ  ትግል ወቅት  ያከናውንዋቸው ከነበሩት መካከል  ባጭሩ፣

- በጦር ሜዳ የተማረኩ የደርግ ወታደሮች (ከአንድ ግዜም በላይ ቢሆንም) ከራሳቸው ባላነሰ መልኩ ተንከባክበው፣ ቁስለኞችን አክመው፣ አስተምረው ፣ ስንቅና መሳፈሪያ የሚሆናቸውን ገንዝብ ሰጥተው ወደ ፈለጉበት ቦታ ይሸኙዋቸው  እንደ ነበር ከተማረኩ ወታደሮችም ሰምቻለሁ፣ በአይኔም አይቻለሁ፣ ከተጻፉት መፃህፍትም አንብቤያለሁ ። የቅርብ ትዝታ በመሆኑ  ደግሞ የአደባባይ ሚስጥር ነው።
- ስልጣን ላይ በነበሩ ገዢ መደቦች ካልሆነ በስተቀር በባለሃብት፣ ነጋዴ፣ የአማራ ሙሁራን ፣የአማራ ተወላጆች   የማጥላላት ስራ ሲያካሂዱ  በቃልም  ይሁን በፅሁፍ ሰምቸም   አንብቤም አላውቅም
- አማራ እንደህዝብ ወይም የአማርኛ ቋንቋ እንደ የአማራ ብሄር ቋንቋ ማንኳሰስ ፣ ማጥላላት የሚባሉ ነገሮች  በቃልም ይሁን በፅሁፍ ሰምቼም  ወይም አንብቤም አላውቅም። እንዲያውም ቋንቋው ሲጠቀሙበት ነበር ማለት ይቻላል።  ይልቁኑ የአማራ ገዢ መደብ  በአማራ ጭቁን ህዝቦች ስም ከመነገድ ባለፈ  ለአማራ ጭቁን ህዝቦች  ያደረጉላቸው ነገር እንደ ሌለ በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጠውል።  ለዚህ በቂ ማሳያ የሚሆነን   በስሙ ይነገድበት የነበረው የአማራ ገበሬ የአኗኗር   ዘዴ መመልከት ነው (እስከ አሁን እንደ ችግር ሁኖ የሚታይ  ከብትና ሰው አብሮ ከማደር ማላቀቅ ያልቻሉ ናቸው)፣ የወሎ ድርቅ  ወዘተ ህያው ምስክር ናቸው ይሉ ነበር።

የህወሓት የትግል አላማ ሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚያቅፍ በመሆኑና በመሆኑ፣ ተቀባይነቱም የላቀ  ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የደርግን ያህል ግዙፍ ሰራዊት በሽምቅ ውግያ የማሸነፍ ምስጥር   አላማቸው ነበር  ብል ማጋነን አይሆንም ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦች እኩልነት፣ ፍትሃዊ ተጥቃሚነት   የሚያምኑ ሰዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው የታጋይ ሃይሎች  ክንድ እየፈረጠመ መጣ።  ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆንም የደርግ  ስርዓት እንደ ስርዓት ግብዓተ መሬት እንዲገባ ሆነ።

### 3.3ከደርግ ወድቀት በኋላ የታዩ ለውጦች

የደርግ ስርዓት እስከ ወደቀበት ድረስ፣ ህወሓት በወታደራዊ ና በፓለቲካዊ ፍልስፍና የማይተካ ሚና ነበረው ቢባል ማጋነን ኣይሆንም። ከደርግ ውድቀት በኋላ ግን የህዝቦች ፍላጎትና ህገ መንግስቱን መሰረት ባደረገ የኣስተዳደር ክልል ተመሰረተ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ራስ የማስተዳደር ስርዓት ተገነባ። እያንዳንዱ ክልል

- የራሱ በጀት ያስተዳድራል ፣
- የፀጥታ ሃይል (ልዩ ፓሊስ፣ መደበኛ ፖሊስ፣ ሚሊሻ ወዘተ) ያደራጃል
- የመንግስት የመዋቅር ስርዓት በክልሉ ይዘረጋል
- በየክልላቸው ያለው ሃብት የመቆጣጠርና የማስተዳደርም መብት ኣላቸው
- ፍትህ በራስ ቋንቋ እንዲሆን ተደርገዋል እንዲሁም ሌሎች ለህብረተ ሰቡ የሚሰጡ ኣገልግሎቶች በቋንቋቸው እንዲያገኙ ተደርጋዋል ወዘተ
- ኣንድ ሰው ካጠፉ በጥፋቱ ልክ በፍርድ ቤት ችሎት የማስኬድ ስርዓት በኣግባቡ ተጀምረዋል ለማለት እደፍራሎህ ። ለምሳሌ የደርግ ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደረገ ። ከዚያም በኋላ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ታይተዋል። በዚህም መሰረት ፍርድ የማስቻል ችሎት ተካሂዶ የፍርድ ቤት ውሳኔ ኣረፈበት። የቅጣት ግዜያቸው ከጨረሱ በኋላ ደግሞ ይቅርታ ተደርጎላቸው ከህብረተ ሰብ ጋር ተቀላቅሎ እየኖሩ ነው።

እንደ እውነት ከሆነ ወንጀልን ማእከል ኣድርገን ከሄድን በሃይለ ስላሴ የነብሩ ሹማምንቶችና በደርግ ባለስልጣናት በፍፁም ኣይገናኙም። ደርግ ግን በኣንድ ጀምበር ነው የኣፄ ሃ/ስላሴ ባለስልጣናት የረሸኑዋቸው።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ብሄራዊ ጭቆና እንደነበር በተለያዩ ወቅት ተገልፀዋል። ስለዚህ የኣመሪካ ወይም የካናዳ ሞዴል ሳይሆን ለችግራችን መፍትሄ ሊሆን የሚችለው፣ የራሳችን ችግር በራሳችን ሞዴል ነው መሆን ያለበት። በዚህም መሰረት የችግሩ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ብሄር ብሄረ ሰቦች ራሳቸው የመወሰን ስልጣን መብት እንዲጎናፀፉ ማድረግ እንደሆነ መገንዝብ (እንዲያውም እስከመግንጠል ድረስ) ይቻላል ። ይህ ማለት ደግሞ የመጨረሻ ውሳኔ ነው ለማለት ግን ኣንችልም። ምክንያቱም የተለያዩ ክልሎች በፍላጎት ኣንድ ክልል /መንግስት መመስረት ከፈለጉ የሚከለክል ህግ የለም።

ስለዚህ አሁን ያለው አከላለል የህዝቦችን ፍላጎትና ከነበረው ብሄራዊ ጭቆና ሊያናግፍ በሚያስችል መልኩ እንደሆነ ያሳያል።

ስለዚህ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖረን ማስቻል ይመስላል። በመሆኑም አንድ ቡዱን ቆርሶ ለሌላ የሚሰጥ /የሚያሳንስ / የሚቀንስ አካሄድ በኢትዮጵያ የለም ብል ማጋነን አይሆንም። በዚህም መሰረት የህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 ዋና አላማ ብሄር ብሄረ ሰቦች እንዲገነጣጠሉ አይደለም ። ህብረተ ሰቡ ራሱ የአንድነት ጥቅም እንድያውቅና እንዲረዳ ማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ በህብረተ ሰቡ ፍላጎትና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነታችንን ወደ ማይናጋ ደረጃ ለማድረስ ታስቦ እንደሆነ እረዳለሁ። መታወቅ ያለበት የግዛት አንድነት አስተሳሰብ አልሰራም ሳይወድ በግድም ቢሆን ለሌላ አስተሳሰብ አስረክበዋል። በእርግጥ ከፌዴራል ስርዓት መዋቀር በኋላ የታዩ ክስተቶችና ለውጦች

- ብናምንም ባናምንም ህወሓት በፌደራል መንግስት የነበረው ሚና ከግዜ ወደ ግዜ እየቀነሰ የሄደ ይመስለኛል።
- ቀና ብለን ብንመለከት በጣም ወሳኝ ይባሉ ከነበሩ የፌዴራል መንግስት የስልጣን ቦታዎች ህወሓት የለም ማለት ይቻላል
- በሌላ መልኩ ሲታይ የአገራችን ኢኮኖሚም እያደገ እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም። ይህንን እየፃፍኩኝ ባለሁበት ሰዓት የሰማሁት ዜና ልገራችሁ። በደርግ የነበረው የአገሪቱ ጠቅላላ በጀት 4 ቢልዮን ብር ነበር። አሁን ወደ 320.8 ቢዮን ብር አድገዋል። ከኬንያ ለመጅመርያ ግዜ በ GDP እኛ እንደ በለጥን ተበስረዋል።

### 3.4 በሰዎች የሚንፀባረቁ አሉታዊ አስተያዬቶችና ድርጊቶች

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የተለያዩ አስተያየትና አስተሳሰብ እየተሰነዘረ ይገኛል። የሚሰጡ አስተያዬቶች ሚዛን የሚደፉ ናቸው ለማለት አልችልም። በ 2008ዓ/ም የተከሰተውን አመፅ መሰረት በማድረግ ግን እየተንጸባረቀ ያለው ሃሳብ ማንሳቱ ጠቃሚ ነው እላለሁ። አስተያዬቶቹም በቀጥታም ቢሆን በተዘዋዋሪ በትግራይ ህዝብ ያነጣጠሩ ናቸው ብል ማጋነን አይሆንም። ከነዚህም

#### 3.4.1 በትግራይ ተወላጆች የሆኑ ባለሃብቶችና ነጋዴዎች በተመለከተ

እኔ እንደሚገባኝ  በኢትዮጵያ ውስጥ ከተለያዩ ብሄር ቤረ ሰቦች ብዙ ባለ ሃብቶች/ፀጎች ተፈጥረዋል። ባለ ሃብቶቹ ያለ አግባብ ያካበቱት ሃብት ከሆነ ለሁላችንም ስለ ሚጎዳ መልካም አይደለም። ሰርተው ያካበቱት ከሆነ ደግሞ የኛም ነው/ ለኛም ፀጋ ነው እላለሁ። በዚህ ሂደት ላይ  የትግራይ ተወላጆችም እንደ ሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች ተወላጅ የሆኑ ባለሃብቶች ይኖራሉ አምናለሁ። እየተካሄደ የነበረውና አሁንም በመካሄድ ላይ ያለው ዘመቻ ግን  የኢትዮጵያ ሃብት በሙሉ በትግራይ ተወላጆች ብቻ እንደተወሰነ/ እንደሆነ ነው። ስለዚህ

- የትግራይ ተወላጆች  ብቻ ናቸው በወንጀል ጀልባ ተሳፍረው ለመበልፀግ የቻሉን? ወይስ
- በራሳቸው ጥረት በአገራቸው እንደሌሎች ሰርተው መበልፅግ አይችሉምን?

ለእኔ እንደሚገባኝ  ባለ ሃብቶች  የየተኛው ብሄር ብሄረ ሰብ ተወላጅ ሊሆን ይችላል። በላቡ ያገኘው ሃብት ከሆነ የሚያኮራ ነው። ልንደግፈው ልናበረታታው ይገባል። ያለአግባብ ከሆነ  የበለፀገው ደግሞ  በሄሩ ሳይሆን መረጃዎቹ ናቸው  መጉላት ያለባቸው ። ይህ በማድረጋችን ደግሞ ተያያዥ ጉዳዮችን ማሳየት እንችላለን ።  በመሆኑም በየተኛውም የህብረተ ሰብ ክፍል  ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት ነው።

በመረጃ ካልተመሰረተ ግን ልዩነትን ያሰፋል፣ የብሄር ተኮር ጥቃት መልክ ይይዛል ውጤቱም ለየተኛውም ወገን አይበጅም።

### 3.4.2 በ 2008ዓ/ም በጎንደር ላይ የነበረው ግርግርና ናፍጣዎቹ

ከሃምሌ-ነሃሴ 2008 ዓ/ም ጎንደር ላይ ግርግር መፈጠሩ ይታወሳል።  በግርግሩ ጊዜ ይወሩ የነበሩና በጆረየ የሰማሁዋቸው ላውራችሁ። በሃምሌ መጀምርያ አካባቢ ኮነሬል ደመቀ የተባለ ግለ ሰብ በመንግስት ተፈለገ። መንግስት የፀጥታ ሃይሎች በማሰማራት ግለሰቡን ለመያዝ ፈለጎ፣ ባቀደው መሰረትም  የፀጥታ ሃይልሎች አሰማራ ። በዚህ ወቅት በጎንደር ከተማ ይወራ የነበረው ላካፍላችሁ፣

- በአሁኑ ሰዓት  የትግራይ  ፓሊሶች  ከተማችን እያናወጥዋት ነው
- ትግራይ ላይ (ሽረ፣ መቐለ፣ አኩስም ወዘተ) የአማራ ተውላጆች እየተገደሉ ነው። አገዳደሉም ቤንዚን አርከፍክፈው ነው የሚያቅጥሉዋቸው

- “ትግ “ የምትል ታርጋ ያላት መኪና የትግራይ ልዩ ፖሊሶች ይዛ ጎንደር ገብታለች
- የአማራ ተወላጅ ንብረት የሆነች አውቶብስ ሽሬ ላይ ተቃጥላለች
- ዳሽን ቢራ መቐሌ ላይ ስድስት ብር ሲሆን ጎንደር ላይ ከአስራ ሁለት ብር በላይ ነው ወዘተ

የበሬ ወለደ ዓይነት ነበር ወሬው። የማይወራ ወሬ አልነበረም። ሁሉም ነገር ከትግራይ ጋር ነበር የሚያያዘው። እውነቱን ለማውራት ከሆነ የፌዴራል ፓሊስ ነበር ግለሰቡን ለመያዝ የሞከሩት። ወሬው ግን የጦዘና እጅግ የሚያሳፍር ነበር። በትግራይ ክልል ውስጥ አንድም የአማራ ተወላጅ መሞት ይቅርና አማራ በመሆኑ ብቻ የተንገላታ የለም። በእርግጥ በጎንደር ከተማ በትግራይ ተወላጆች ላይ ግፍ እየተፈፀመ ነበር። ምን ያህል አስከፊ እንደነበር ለመረዳት “ኢትዮጵያን ማነው የሚያስተዳድራት” በሚል ርእስ በኣይጋ ፎሮም ፖስት ተደርገዋል ማንበብ ይቻላል።

በከተማዋ የተቀጣጠለው ውዥንብር እየተነዛ የነበረበት ምክንያት በትግራይና በአማራ ተወላጆች እንደ ብሄር ግጭቱ እንዲባባስና ወደ ለየለት የብሄረ ሰብ ግጭት እንዲለወጥ ሆን ተብሎ የተሰራ ይመስላል ። ያልተደረገ ተደረገ፣ ያልተሰራ ተሰራ ወዘተ።

### 3.4.3 በልማት መውቅራዊ ይዘትና የሚስተጋባው ወሬ

በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የፌዴሬሽን ም/ቤት በሚቅርበው ቀመር መሰረት እያንዳንዱ ክልል የበጀት ድጎማ ያገኛል። በጀቱ ጥቅል በጀት በመሆኑ ክልሎች የክልላቸውን ህብረተ ሰብ ፍላጎት መሰረት ባደረገና ከአጠቃላይ የአገሪቱ የልማት እቅድ በማጣጣም ጥቅል በጀቱ በራሳቸው መንገድ መመደብ ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ በጀቱ በስራ ላይ የማዋል ጉዳይና የህብረተ ሰቡ ተጠቃሚነት የየክልሎቹ የቤት ስራ ነው የሚሆነው። እንደ አፄዎችና ደርጋውያን በፈለጉት አካሄድ የሚሰራጭ በጀት የለም በአሁኑዋ ኢትዮጵያ። ጥሩም ሆነ መጥፎ በክልሉ የመንግስት ሃላፊዎችና ህዝቡ ትክሻ ላይ የወደቀ ነው።

በፌደራል ደረጃ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አሉ። እነዚህ ደግሞ በግልፅ የሚታወቁ በመሆናቸው ማንም ሰው ሊፈርድ ይችላል። ፕሮጀችቶቹ በኣመዛኙ በኣዲስ ኣበባና ኣከባቢዋ ፣ ጁቡቲ መስመር፣ አባይ ግድብ ወዘተ ናቸው ትላልቅ ፕሮጀችቶች ብለን የምንጠራቸው።

በመንግስት በኩል በትግራይ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከላይ ያዬነው ጉዳይ ነው። ነገር ግን የአማራ ገዢ መደብ አቀንቃኞች በትግራይ ክልል ምንም የልማት ድርጅቶም የሚባሉ መኖር የለባቸውም፣ የእንድስትሪ ጭላንጭል መኖር የለበትም ፣ ትግራይ በምንም መልኩ ወደ ስልጣኔ ጎራ መቀላቀል የለባትም፣ የትግራይ ህዝብ በላቡ ሰርቶ እንዲበላ ካለመፈለግ ይመስለኛል አይናቸው ወደ ትእምት እንቅስቃሴ ነው የሚያሾረው። ለማነፃፀር ያህል በሌሎች ክልሎች ተመሳሳይ ተቅዋሞች አሉ። ነገር ግን በሌሎች ክልሎች ያሉ ተመሳሳይ ተቅዋማት እያነሱ ሲኮኑ አይሰሙም። ትግራይ ላይ ሲሆን ግን አይናቸው ደም የሚለብሰው። እንግዲህ ዘረኛ አስተሳሰብ መባል ያለብት የነዚህ ወገኖች አስተሳሰብ ነው። እንደህዝብ ሰርተን የመበልፀግ መብት ለማሳጣት ሌት ተቀን ሲባዝኑ ይታያሉ።

ስለዚህ ትግራይ የኢትዮጵያን ሃብት በመውሰድ ከሌላ ክልል በላይ አድጋለች ተመንድጋለች የሚል ወሬ ያሰማሉ። ያለምንም መረጃና ማስረጃ የሚስተጋባው ወሬ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው የሚል ጥያቄ ያስጭራል? የትግራይ ህዝብ እንደህዝብ በኣሁኑ ሰኣት ዘንቶት፣ ሁሉም ነገር ተመቻችተዋል ማለት አልችልም። በየተኛውም የኢትዮጵያ ኣካባቢ ያለው ችግር ትግራይ ላይም ኣለ ለማለት እደፍራሎህ። የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተሸከመው ትልቅ ጫና ግን ኣለ።

- ከኤርትራ ጋር ያለው ችግር በትግራይ ላይ በኢኮኖሚም ሆነ በማህበራዊ ኑሮ ከፍተኛ ጫና ደርሶበታል እየደረሰበትም ነው ያለው።
- ይሉኛል በሚል የህወሓት ፖሊሲ ከፌዴራል መንግስት ማግኘት ያለበት ጥቅም እያገኘ አይደለም (ለምሳሌ ኣቶ ኣባይ ወልዱ በግንቦት ወር ከፌደራል መንግስት ወደ ትግራይ ከመጡ ባለስልጣናት ያደረጉት ንግግር በቂ ማስረጃ ነው፣ ኣቶ ኣባይ በትግራይ በፌዴራል በኩል የተሰራ የመስኖ ግድብ እንደሌለና በሌሎች ክልሎች መሰራቱንና ጥቅም ላይ መዋሉን ጠቅሰዋል)። እስከኣሁን ያለት ክንውኖች የሚያሳዩን በፌዴራል መንግስት በትግራይ ላይ የሚሰራ ከሆነ ሌላው ካዳረሱ ነው ወደ ትግራይ የሚመጡት። (የተሰራም የሚስራም ከሆነ ማልቴ ነው (ለምሳሌ ከኣዲስ ኣበባ የሚነሳው ዋና መንገድ ትግራይ ላይ በጣም ዘግይቶ ነው የተሰራው)።

የሚናፈሰው የማጥላላት ወሬ ብቻ ለትግራይን ህዝብ እየመገበው ይገኛል። ለትግራይ ህዝብ ምን እያሉት እንደ ሆነ ግን በጣም የሚገርም ነው!!!!! በጣም የሚያሳዝን ይመስላል። ወደ ማጠቃለያ አስተያዬቴን አስቀምጣሎህ።

### 3.4.4 በፍትህ አካላትና ማህበራዊ አገልግሎት ያለው መዋቅርና የሚስተጋባው ወሬ ንፅፅር

እያንዳንዱ ክልል የራሱ የሆነና በክልሉ የሚታዘዝ፣ የሚሾም የፀጥታ፣ የፍትህና የአገልግሎት ተቋዋማት ያቋቁሟል ። ብዛታቸውም እንደየ ክልሉ አቅም ሊለያይ ይችላል። የፍትህ ፣ የዲሞክራሲ፣ የአገልግሎት ፣ የፀጥታ ስራዎች በየክልሉ የሚዋቀሩ ናቸው። የአማራ ክልል እንደምሳሌ ብንወስድ ፣

- <u>**ፍትህ ና ዲሞክራሲ በተመለከተ**</u> ፥ የክልሉ የፍትህ ፕሬዚደንት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉት ተቋዋማት በክልሉ የሚቋቋሙ ናቸው። ብዛታቸውም እንደ ክልሉ ስፋት ይወሰናል። በየቦታው የሚቀመጡ ሰዎችም የክልሉ ተውላጆች ናቸው። ስለዚህ አንድ የአማራ ተወላጅ በወያኔ ፍትህ አጣሁ ቢል በጣም ይገርማል። ፍትህ የማጣቱ ጉዳይ እውነት ሊሆን ይችላል። ጣቱ የሚቀስረው ወዴት ነው የሚለው ግን ያጠያይቃል። መጠየቅ ካለበት ክልሉ የሚመራው መንግስትና ፓርቲ (ብአዴን)መሆን ይገበዋል።
- <u>**ፀጥታ በተመለከተ፥**</u> ክልሉ ከልዩ የፓሊስ ሃይል ጀምሮ መደበኛ ፓሊስ፣ ሚሊሻ፣ ኮሚኒቲ ፖሊስ ያቋቁማል። ስለዚህ በወንጀልም ወይም ያለ ወንጀል ከሆነ አንድ ሰው የሚታያስረው በክልሉ የተዋቅረ የጽጥታ ሃይል ነው። አንድ የአማራ ተወላጅ በወያኔ ታሰርኩ ቢል በጣም ይገርማል። መታሰሩ ያለ መታሰሩ ጉዳይ አይደለም። ጣቱ የሚቀስረው ወዴት ነው የሚለው ግን ያጠያይቃል። መጠየቅ ካለበት ክልሉ የሚመራው መንግስትና ፓርቲ (ብአዴን) መሆን ይገበዋል። እንዲያውም ህገ መንግስቱ ለክልሎች የሚሰጠው መብት እንደ ሚከተለው ነው። የክልሉ መንግስት በአካባቢው ያለው የፀጥታ ችግር ከአቅሜ በላይ ነው ካላለ የፊዲራል መንግስት ጣልቃ አይገባም ይላል። መታወቅ ያለበት በፌዴራልና በክልል መንግስታት የላላ ግንኙነት መኖሩን ያመለክታል።
- <u>**ማህበራዊ አገልግሎት፥**</u> የጤና ፣ የትምህርት፣ የአስተዳደር ወዘተ የመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚቋቋሙት በክልሉ ያለው መንግስት አማካኝነት ነው። በጤና

፣ በትምህርት  ወዘተ በሁሉም ክልሎች እንደ የአካባቢያቸው ሁኔታ አገልግሎት ይሰጣል። ይህ ደግሞ የሚመራው በክልሉ መንግስትና ፓርቲ(ብአዴን) ነው። ባለሙያዎች ሆነ አገልግሎት ሰጪዎች የክልሉ ተወላጆች ናቸው ። ስለዚህ አንድ የአማራ ተወላጅ ወያኔ ጤና አላስፋፋም፣ እናቶች እንዳይወልዱ ተደርገዋል ቢል በጣም ነው የሚገርመው። ጭግሩ ሊኖር ይችላል አላውቅም ። መወቀስ ካለበት ግን ማን ነው?። ስለዚህ ጣቱ የሚቀስረው ወዴት ነው የሚለው ግን ያጠያይቃል። መጠየቅ ካለበት ክልሉ የሚመራው መንግስትና ፓርቲ (ብአዴን) መሆን ይገበዋል።

ስለዚህ በአማራ አንድ ሰው ቢታሰር፣ ፍትህ የሚያገኘውም እዚያው ነው። ወደ ትግራይ አይመጣም። በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ በምንም መልኩም ቢሆን ህወሓት በአማራ ክልል ጣልቃ ገብቶ ወንጀለኛው የሚያስረው፣ ፍትህ የሚያዛባው፣ የጤና አገልግሎት የሚስተጓጉልበት ወዘተ ማክንያት የሌለና ወሬው ፈጠራ መሆኑ ግንዛቤ መያዝ ያለብት ይመስለኛል። ስርዓቱ የተዋቀረው ከላይ በተገለፀው መልክ ነው።

### ለምንድ ነው በትግራይ ተውላጆች ላይ ጫና የሚፈጠረው?

### 3.4.5 በፌዴራል የትግራይ (ህወሓት) ውክልና እና የሚወራው ወሬ ንፅፅር

ትግራይ እንደ የኢትዮጵያ አካል በፌዴራል ደረጃ ውክልና መኖር ግድ ይላል። እውነታው ይህ ሁኖ እያለ ግን  በፌዴራል መንግስት የሌላ ብሄር ብሄረ ሰቦች ውክልና እንደሌለ አስመሰሎ ያወራሉ። ነገር ግን ፣

**በፌዴራል ደርጃ ባሉት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች በብሄር ተዋፅኦ ስብጥር የየተኛው ብሄር ነው ሚበዛው?**

ይህን ጥያቄ መነሻ አድርጎ በፌዴራል የመንግስት መስርያ ቤት የተያዙ ቦታዎች የብሄር ተዋፅኦ  ለመረዳት የብሄር ንፅፅር ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ከትግራይ የተወከሉ ብዙ ከሆኑ ወሬ ሳይሆን እንደግባት ይቆጠራል። እየሆነ ያለው ግን  ሙሉ በሙሉ የስልጣን መዋቅራዊ ይዘቱ በወያኔ  (ህወሓት) እንደተያዘ አድርጎ መሳል  ነው። ለኔ እንደ ሚመስለኝ  በድሮ ሳይሆን አሁን ባለው መዋቅር ትችታችን መሰረት ቢያደርግ መልካም ነው።  ስለዚህ ልንግርበት እንችላለን ።  ካልሆነ ግን የትግራይ ህዝብ እንደ

ህዝብ ደርግን ለመጣል ከፍተኛ መስዋእትነት ከፈለ እንጂ ከሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች የተለየ ጥቅም አግኝተዋል ብዬ ኣላስብም። የተከፈለው መስዋእትነት ታሳቢ ኣድርገን የምንተች ከሆነ ደግሞ በግልፅ የኣማራ ገዢ መደብ ለመመለስ የሚደረግ ጥረት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በትግራይ ህዝብ ያላቸው ጥላቻ ከመግለፅ ባለፈ የዚህ ዓይነት ማጥላላት እርባና የለውም ።

ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ የዘረኛ ፖለቲካ ኣራማጅ ነው ይላሉ? ኢትዮጵያን በዘር ከፋፍሎዋታል ይላሉ ወዘተ እነዚህ ምንድ ነው መልእክታቸው ወደ ማጠቃለያ ኣስተያዬቴን እሰጣሎህ። ስም ከማጥቆር ኣልፎ በ 2008 ዓ/ም ላይ ጎንደር ላይ በተካሄደው ኣመፅ ለብኣዴን ምንም ሳይሉ በወያኔ የኣመራር ኣካላት ላይ ብቻ በማተኮር የተለያዬ የስድብ ናዳ ያወረዱት፣ ፎቶ ያቅጠሉት። ስለዚህ ሰፋ ያለ መረጃ ለማግኘት " ኢትዮጵያን የሚይስተዳድረው ማነው? " በሚል ርእስ በኣይጋ ፎሮም ፖስት የተደረገውን ማንበብ ይቻላል።

### 4. ማጠቃለያ

የታሪክ ኣጋጣሚ ሁኖ በኢትዮጵያ ኣፄዎችና ደርጋውያን ብሄርን/ ዘርን መሰረት ኣድርገው የፈፀሙትን ጭካኔ የተሞላበት ግድያ፣ መስለብ፣ ማረድ ፣ መቁረጥ ኣይተናል። ከዚህ በተጨማሪ ከኣፄዎችና ደርጋውያን ብሄር/ዘር ውጭ ሌላው እንደሰው ያለመቁጠር፣ በሌላ ብሄር የባህል ጫና መፍጠር ፣ በስነ ልቦና መጉዳት ወዘተ ለማየት ችለናል። የመሪዎቹና ተከታዮቹ ድርጊቶች የሚያሳዩት በዘረኝነት ማእበል ዋኝተው እንደ ነበር በግልፅ ያሳያል።

ኣፄዎቹና ደርጋውያን በወቅቱ ድል ያደረጉ ቢመስላቸውም ለኢትዮጵያ ግን እንደ ኣገርም፣ እንደ ህዝብም የጠቀመን ነገር የለም። ይልቁንስ እስከ ኣሁን ድረስ

- ❖ ሁለት ታላላቅ የሆኑ ታሪካዊ ኣሽራዎቻችን ኣጥፍተዋል ወይም ደግሞ እንዲደብዝዝ ኣድርገዋል እነሱም፥
  - ✓ የኣኩሱም ስርወ መንግስት በስልጣኔ ማማ ላይ እንደነበር ማንም የሚመሰክርለት ነው። በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ የኣኩሱም መንግስት ከወደቀ በኋላ የስልጣኔው ኣሻራዎች በዛጉዌ ስርወ መንግስት በላሊበላ ውቅር ኣብያተ ክርስትያናት ለመንፀባረቅ ችለው ነበር። ስልጣን ወደ ሸዋ ኣፄዎች ከተላለፈ በኋላ ግን የዘላን

መንግስት ነበር  የተቋቋመው ብንል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም ከ 1270 አካባቢ ጀምሮ ወደ 700 ዓመታት ያክል በስልጣን ቆይተዋል። በዚህ ረዥም ዓመታት የወሰደ የስልጣን ዘመናቸው የአኩሱምና የዛጉዌ  መንግስታት ስልጣኔ ማሳደግ ወይም ማስቀጠል ብቻል  ኑሮ ዛሬ  መፅዋቾች እንጂ ተመፅዋቾች አንሆንም ነበር ።

✓ የዴሞክራሲያዊ እሴቶቻችን አደብዝዘዋል። የኦሮሞ ህቦች ይጠቀሙበት የነበረው የገዳ ስርዓት ከነበረው ወቅት ሲነፃፀር እጅግ ዲሞክራሲያዊ የባህል እሴታችን መሆኑን እንረዳለን። የገዳ ሰርዓት ቀጣይነት ባለው መልኩ ቢቀጥል ኑሮ ዛሬ ስለ ዲክራሲያችን  ምእራባውያን የሚያፌዙቡን ሳይሆን  እኛ  ነበረ የምናስተምራቸው።

ስለዚህ አፄዎቹና ደርጋውያን ትልቅ የአእምሮ ብስለታቸው፣ ራሳቸው  በፈጣሪ የተመረቁ ሌላው ደግሞ የነሱ አገልጋይ አርገው ያስቡት ነበር ማለት ይቻላል። በመሆኑም ማንነታችን ለማስከበር በእርስ በእርስ ጦርነት እንድንዋዥቅ አድርገዋል ። ኢትዮጵያን የመሰለች በስልጣኔና በዲሞክራሲ  ማማ ላይ የነበረች ኣገር ወደ ዘላን የመንግስት ኣስተዳደር እንድትወድቅ ኣደረጉ። በእርግጥ ምንሊክ የውጭና በውጭ የተሰራ ዘመኑን ያፈራ ቴክኖሎጂ ወደ  ኣገር ውስጥ እንዲገባ ፈቅደዋል። ቢሆንም ቅሉ ምንሊክ የተኩ ንጉስ ሃይለስላሴ በፊውዳላዊ ስርዓት ኣገዛዝ ኢትዮጵያን ኣራቆትዋት ። ወደ ጦርነት ኣውድማ እንድትገባ መንገድ ከፈቱ።

ከደርግ ውድቀት በኋላ ኢትዮጵያ በፌደራል ስርዓት እንድትተዳደር መንገድ ተከፍተዋል። ኦሮም እንደ የኦሮሞ መንግስት፣ ኣፋር እንደ የኣፋር መንግስት፣ ቤንሻጉል እንደ የቤንሻንጉል መንግስት፣ ወዘተ ተዋቅረዋል ። በኣሁኑ ሰዓት የተገነባው የመንግስት መዋቅር በጣም ጥቂት ከሚባሉ የአማራ ገዢ መደብ ኣስተሳሰብ ከሚያራምዱ ሃይሎችና ተከታዮቻቸው በስተቀር ሁሉም በደስታ የተቀበለው የፌደራል የመዋቅር ስርዓት ነው። ክልሎች የመንግስት ስርዓት ኑሩዋቸው፣ በጀት የማስተዳደር፣ የፀጥታና የፍትህ ተቋዋማት መምራት፣ ትላልቅ ፕሮጀችቶች የመምራት ባህል ኣሳድገዋል።  እውነታው ይህ ነው።

ነገር ግን ኣሁንም በበሪ ወለደ  ፕሮፓጋንዳ ተልእኮዋቸው ለማስፈፀም ላይና ታች ይላሉ። በተለይ በትግራይ ህዝብና መንግስት የማያነሱት የማይነዙት ወሪ  የለም። ወሬው

የሚጨበጥ ኣይደለም። ተኝተው ያለሙት ሁሉ ይፅፋሉ። በወሬውና ማጥላላቱ የምንለው ነገር " ኣያ ጅቦ ሳታማኸኝ ብላኝ" ነው።

ለምሳሌ በ2008 ዓ/ም በጎንደርና ኣካባቢው በትግራይና ቅማንት ተወላጆች እንዲሁም በምእራብ ጎጃም ኣከባቢ በትግራይ ተውላጆች በብሄራቸው ብቻ የሞራል፣ የስነ ልቦና፣ ቤታቸውና ንብረታቸው መቃጠል፣ የኢኮኖሚ ድቀት፣ የህይወት ማጣት እንደደረሰ የኣደባባይ ምስጢር ነው። የነበረው ኣመፅ መሰረት ኣድርጎ ዩሁኔ በላይ "በኣዲሱ ዘመን. . . . . " ብሎ ከዘፈነው ልጥቀስ " ማንነቴ መልሱ እያለ ሲዘምር ዋለ. . . . ." የሚለው ስንኝ ስንወስድ ምን ያሳል? ወደ የኣማራ ገዢ መደብ የበላይነት ወይም "ደርግ. . . " ይሻለናል እየተባለ መሆኑን ያመላክታል። ጎንደር እና ምእራብ ጎጃም ሁነህ የሌላ ብሄር ተወላጆች በብሄራቸው ለይተህ እየመታህ እያጠቃህ " ማንነቴ መለሱ. . . ." ይገርማል!!! ቢሆንማ ታሪክ ራስዋ ደገመች እንል ነበር ። ከዚህ በተጨማሪ በባህር ዳርና በመቐለ ከነማ የእግር ኳስ ጨዋታ መቐለ ላይ እንደነበር ይታወሳል። በጨዋታው ወቅት ችግር ተፈጥረዋል። የችግሩ መንስኤ ማን ይሁን ምን ችግሩ በመፈጠሩ ብቻ ማዘን ይገባናል። በእግር ኳስ ጨዋታ ችግር እንደሚያጋጥም በኣውሮፓም ቢሆን የምናየው ጉዳይ ነው። ዘ-ሃበሻ የሚባለውን ማህበራዊ ድህረ ገፅ ግን ችግሩ ለማባባስ እየሰራ ነበር። ይንፀባርቁ ከነበሩት መካከል " መቐለ የደም መሬት ፣ ኣማራ ተኝተሃል" . . . . . . ወዘተ ። የሚያሳዝን ዘገባ። ለማን እንደሚመች ግን ኣልውቅም።

ስለዚህ ቆም ብለን እናስብ ድርጊቶችን እናመዛዝን፣ ውሳኔ ላይ እንድረስ። በዘረኝነት ኣባዜ እየዋኙ ያሉ ግለ ሰቦች ስለ ኢትዮጵያ ኣንድነት በሚመለከት ሲመፃደቁ ይታያሉ። ኢትዮጵያ በዘር ተከፋፈለች፣ ተለያዬን ወዘተ። ሃስባቸው በጣም ይሰቀጥጣል፣ በኣንድ በኩል ኣንድ ብሄር ማእከል ኣድርጎ የማጥላላት ዘመቻ ማካሄድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ኣንድነት ማውራት ነው። ከታሪካቸው የምንረዳው ፣ በነሱ ኣመለካከት የኢትዮጵያን መሬት እንጂ ህዝቦችዋ ግምት ውስጥ ኣያስገቡም። ይህንን የሚያጠናክርልን ደግሞ ከኤርትራ መንግስት ኣብረው መስራታቸው ነው። የኤርትራ መንግስት በየተኛው መለክያም ቢሁን የኢትዮጵያ ጥቅምና መብት ለማስከበር ይቆማል ብሎ ማሰብ ሞኘነት ነው። ስለዚህ ከኤርትራ መንግስትና ከግብፅ ጋር እየተዋዋሉ የነሱ ኣሽክር ሁነው ፣ የነሱን ኣላማ ለማስፈፀም ቃል ገብተው ስለ ኢትዮጵያ ኣንድነትና ጥቅም ማውራት የሚታሰብ ኣይመስለኝም፣ ወድቀት እንጂ።

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ አንድን ብሄር የሚጠላ፣ የማግለል ስራ የሚሰራ ፣ ወዘተ በየተኛው መልኩም ሌላኛው ብሄር ወይም ብሄረ ሰብ ሊወድ አይችልም። ማሸነፍ ከቻለ የተፈጥሮ ባህርይ ነውና በየተኛውም በሄር ብሄረ ሰብ ታሪካዊው ስራው ሊያደሰው እንደሚችል (እንደኢትዮጵያውያን) ታሪካችንና ድርጊታችን በግልፅ ያስረዳል። ለምሳሌ "ማንነቴ መልሱ እያለ. . . . .' የሚለው ዘፈን ትክክለኛ ነፀብራቅ መሆኑን ያሳል።

በህወሓት በኩል ግን ዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት እንጂ ዘረኝነትን የሚያሳይ በፅሁፍም በቃልም ማየት አልቻልኩም አልሰማሁምም። አለ የሚል ሰው ካለ ግን ዝም ብሎ ከማጥላላት ፣ ስም የማጥቆር ዘመቻ ሳይሆን ማስርጃው በማጣቀስ በህወሓት ድርጊት ቢያቀርቡ መልካም ነው እላሎህ፣ እኔም እማርበታሎህ። ወሬ ግን ምን ጊዜም ቢሆን እርባና ሊኖረው አይችልም፣ ለኛም እንደ ህገር አይበጅም። ምክንያቱ ከመረጃና ማስረጃ ውጭ የምንሰነዝራቸው ሃሳቦች እንደ ህዝብና አገር ጉዟችን ያደንቅፋሉ ።

ሁሉም ሰው የተሻለ ሂወት፣ መብት እንዲኖረው ይፈልጋል። የተሻለ ህይወት መፈለግ መልካም ነው። በሁሉም ዘርፍ ዛሬውኑ አገራችን እንደ አውሮፓና አመሪካ ብትሆንልን ደስ ይለናል። ነገር ግን ይህ ምኞት ነው ። ምክንያቱ አመሪካና አውሮፓ ከ 200 መቶ አመታት በላይ የሰሩብትና ያዳበሩት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ዲሞክራሲያዊ ተቅዋማት አላቸው። በኛ አገር ሁኒታ ግን ከዛግዌ ስርወ መንግስት መውደቅ በኋላ ፣ ሁሉም ነገር የኋሊዮሽ ጉዞ እንደነበር ወይም ደግሞ እየሆነ መምጣቱን የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። በዚህ ጉዳይ ዶ/ር ሀብተስላሴ በ1986 ዓ/ም በታተመው መፅሃፋቸው በሰፊው ገልፀውታል። ከመፅሃፉ የምንረዳው፣

> **የአማራ ገዢ መድብ ኢትዮጵያን የመሰለች በስልጣኔና በዲሞክራሲ ማማ ላይ የነበረች አገር ወደ ዘላን የመንግስት አስተዳደር እንድትወድቅ በማድረጋቸው ዛሪ መፅዋች መሆን ሲገባን ተመፅዋች የዲሞክራሲ አስተማሪ መሆን ሲገባን የዲሞክራሲ ተማሪ ሁነናል።**

ስለዚህ ለራሳችን ስንል ከታሪካችን ዘረኝነት የውድቀት ምልክት መሆኑን እንገንዘብ !! ምንግዜም ቢሆን ከዘረኝነት የፀዳ አሰራርን እንከተል!! ብሄር መሰረት ያደረግ ጥቃት ይቁም !! ካልሆነ ግን በአንገታችን ላይ ገመድ ማንጠልጠላችንን ከታሪካችን መማር ያለብን ይመስለኛል።

መቀበል ያለብ ጉዳይ **“የጋራ ተጠቃሚነት** “ የሚል ፅንሰ ሃሳብ ነው። የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ከተከተልንና ታሪካችን በትትክል መገንዝብ ከቻልን “ትልቅ ነበርን ትልቅም” እንሆናለን።